**ለአንድ የመዋዕለ ሕፃናት ቦታ ክፍያው ምን ያህል ነው?**
በኖርዌይ የመዋዕለ ሕፃናት የክፍያ ጣሪያ አለ። ይህ ማለት መዋዕለ ሕፃናቶቹ የአገሪቱ ምክር ቤት (Stortinget) በየዓመቱ ከሚወስነው ዋጋ የበለጠ ክፍያ እንዲከፍሉ ወላጆችን መጠየቅ አይችሉም። ከዚህ በተጨማሪ የምግብ ይከፍላሉ። ይህ የምግብ ክፍያ እንደየመዋዕለ ሕፃናቱ መጠነኛ ልዩነት ይኖረዋል።

የመዋዕለ ሕፃናት ቦታ ዋጋን እዚህ ይመልከቱ፡ www.bergen.kommune.no/pris-barnehageplass

አነስተኛ ገቢ ያላቸው ወላጆች ቅናሽ የወላጅ ክፍያ የመክፈል መብት ሊኖራቸው ይችላል።

ለተጨማሪ መረጃ እዚህ ያንብቡ፡ www.bergen.kommune.no/redusert-foreldrebetaling

**የመዋዕለ ሕፃናት ምርጫ እና የመዋዕለ ሕፃናት ቦታ ማመልከቻ**
የመዋዕለ ሕፃናት ቦታን በ www.bergen.kommune.no/barnehageplass ድረ ገጽ ላይ ማመልከት ይችላሉ።

በዲጂታል የማመልከቻ መተግበርያው ላይ (ሰማያዊ አዝራር) ለርስዎ ቅርብ የሆኑ መዋዕለ ሕፃናትን ማግኘት ይችላሉ።

በበርገን የሚገኙ መዋዕለ ሕፃናት ሙሉ ዝርዝር በሚከተለው ገጽ ላይ ያገኛሉ፡

www.bergen.kommune.no/barnehager

ለእርሶ ቅርብ የሆኑ መዋዕለ ሕፃናትን እዚህ ላይ መፈለግ ይችላሉ፡ www.barnehagefakta.no

**ለመዋዕለ ሕፃናት ቦታ ለማመልከት እርዳታ ይፈልጋሉ?**
Kaigaten 4 ላይ ከByparken ፊት ለፊት ወደ ሚገኝ የነዋሪዎች አገልግሎት ክፍል ይምጡ፣ ወይም በስልክ 55 56 55 56 ይደውሉ። የኖርዌይ መታወቂያ ቁጥር የሌለዎትም ከሆነ ለማመልከት እርዳታ በዚሁ ክፍል ያገኛሉ።


*የነዋሪዎች አገልግሎት ክፍል Kaigaten 4. ምስል: ክርስቲን ሃውግ*

BERGEN
KOMMUNE

Foto forside: © Trude Haugen
Skipnes.no Svanemerket trykksak, 2041 0731

AMHARISK

# መዋዕለ ሕፃናት - መልካም ጅምር






## መዋዕለ ሕፃናት - መልካም ጅምር

መዋዕለ ሕፃናት የትምህርት ዓለም መግቢያ በር እና ሕፃናት የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ፣ ጨዋታ እና የመማር ዕድል እንዲያገኙ የሚረዳ ትምህርታዊ ተቋም ነው። እድሜያቸው ከአንድ እስከ ስድስት ዓመት የሆኑ በኖርዌይ የሚኖሩ አብዛኞቹ ሕጻናት ወደ መዋዕለ ሕጻናት ይሄዳሉ።

### መዋዕለ ሕፃናት - ከወላጆች ጋር በቅርብ በመተባበር የሚሰጥ ትምህርታዊ አቅርቦት

ሁሉም መዋዕለ ሕፃናት፣ የግልም ሆኑ የመንግሥት፣ የመዋዕለ ሕፃናትን ሕገ-ደንብ ይከተላሉ። መዋዕለ ሕፃናት የሚቀጠሩት መምህራን ቢያንስ የሦስት ዓመት የኮሌጅ ትምህርት ያላቸው ናቸው። ይህም ማለት ልጅዎ ስለ ሕፃናት ጠለቅ ያለ እውቀት ባላቸው ብቁ ባለሙያዎች እንክብካቤ ይደረግለታል ማለት ነው። ለሕጻኑ/ኗ የሚደረገዉ ክትትል ከቤተሰብ ጋር በሚፈጠር ጥብቅ ግንኙነት አማካይነት ነዉ። ማወቅ የሚፈልጉት ነገር ካለ እና እንዲሁም ለልጅዎ ምቾትና ማህበራዊ ዕድገት የሚረዱ ሀሳቦች ማቅረብ ከፈለጉ ሠራተኞቹን ማነጋገር ይችላሉ። የባህል ልዩነት ሲኖር በመዋዕለ ሕፃናቱ እና በቤተሰብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት ይበልጥ ጠቃሚ ይሆናል።







### መዋዕለ ሕጻናት - የጨዋታ፣ የመማሪያ እና የእድገት ቦታ

- በመዋዕለ ሕፃናቱ ውስጥ ልጅዎ ሌሎች ሕፃናት በሚሳተፉበት ማህበራዊ አካባቢ ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል። ሕፃናቱ እርስ በርስ የባህል፣ የቋንቋ እና የፍላጎት ትውውቅ ያደርጋሉ። ሕፃኑ ከሌሎች ሕፃናትና ከአዋቂዎች ጋር በሚፈጥረው መስተጋብር በጨዋታዎችና በተለያዩ እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ያብባል እንዲሁም ይማራል። ሕፃኑ ጓደኞች ያፈራል፣ ማህበራዊ ችሎታ ያዳብራል፣ በሁሉም የእድገት መስኮች የሚያጠነክሩትን የቅድመ-መደበኛ  ትምህርት ልምምዶችን ያገኛል።

- የሕፃናት የቋንቋ እድገት የሚነቃቃዉ በመዋዕለ ህፃናት ውስጥ ነዉ።  ከሌሎች ሕፃናት ጋር በመጫወት እና ነገሮችን በመመራመር ሕፃኑ የራሱን ሀሳብ፣ አስተያየት፣ ስሜት እና ልምድ ያዳብራል። መዋዕለ ሕፃናቱ ውስጥ የሕፃኑ የቋንቋ ችሎታ የሚያድገውም በዚህ መልኩ ነው።

- ሕፃናት በአንድ ጊዜ ብዙ ቋንቋዎችን መማር ይችላሉ። መዋዕለ ሕፃናቱ ከወላጆች ጋር በመሆን ሕፃኑ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን ከቤተሰቡ፣ ኖርዌይኛን ደግሞ ከመዋዕለ ሕፃናት እንዲማር ሁኔታዎችን ያመቻችለታል።

- ቋንቋን መማር ጊዜ ይወስዳል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አንድን ቋንቋ ተምሮ ከሌሎች ጋር በጥሩ ሁኔታ ለመግባባት ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት የሚወስድ ሲሆን፥ ቋንቋውን ለምሳሌ መደበኛ በሆኑ፣ ማንበብን እና መጻፍን በሚያካትቱ የትምህርት ሁኔታዎች ላይ ለመጠቀም ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት ይወስዳል። ስለዚህ ከመደበኛ ትምህርት በፊት መዋዕለ ሕጻናት ቀደም ብሎ በመጀመር ኖርዌይኛን መማር አስፈላጊ ነዉ።

### መዋዕለ ሕፃናት - ለወላጆች እድሎች ይፈጥራል

- ልጅዎ የመዋዕለ ሕጻናቱ ብቁ እና ጥሩ ተንከባካቢ ሰራተኞች ይዘውት መዋዕለ ሕጻናት መዋሉ፣ ለእርስዎ ለወላጅ ሥራ ለመጀመር ወይም ትምህርት ለመማር እድል ይፈጥርሎታል።

